# ሰሞኑን በፓልቶክ
# ቁጥር ሶስት
# ማዘር

ከበልጅግ አሊ

„ኢሕአፓ መግደል አልጀመረም ገሎ ሬሳ መሸጥ የጀመረው ደርግ ነው ።ለምሳሌ ዳሮ ነጋሽን ሲገድል ዳሮ መሳሪያ ይዛ አልነበረም የተገኘችው። የተገደለችው የመብት ጥያቄ በማቀረቡዋ ነበር ። “
ማዘር

በተከታታይ ስለፓልቶክ ለማቅረብ ለራሴ ቃል በገባሁት መሰረት ለእኔም የሰሞኑን ሱሴን ለመወጣት ለእናንተም ሪፖርቱን ለማቅረብ እፓልቶክ ውስጥ ወጣ ገባ ስል ነው የከረምኩት። አዲስ ነገር ፍለጋ ካንዱ ወደ አንዱ ክፍል እየተሯሯጥኩ ብከርምም ያገኘሁት ነገር ብዙም አዲስ አደለም። አዲስ ነገር ቢኖር የደደቦች ሸንጎ አጋፋሪዎች የወያኔ አንቀላፊነት ጥርጥሬዬን የበለጠ አጠናክሮልኛል።አንዱ አጋፋሪ ጠቅላላውን የትግራይ ህዝብ እንደጠላት የመደበ ሲሆን ይህም አባባሉ በዐይጋ ፎሩም ተጠቅሶ ለአድማጭ ቀርቦል ። ግለሰቡ ይህንን አጥቶት አይመስለኝም ከራሱ ከዐይጋ ፎረም ታዞ ካልሆነ በስተቀር።

የማታ አፍ ከጋን ይሰፋል እንዲሉ በየምሽቱ በኢሕአፓ ላይ ሲላቀቅ የከረመው የድጋፍ ወረቀት አርበኛ የዕውቀት ደረጃ በፈቀደለት ይህንን አፀያፊ ንግግር ቢያደርግ ምን ሊገርመን ። በሌሌች ክፍል የነበሩ ታዳሚዎች በዲያስፖራ ክፍል ተሰብስበው ሁኔታውን ተወያይተው ይህንን አላፊነት የጎደለው አባባል አውግዘው ተለያይተዋል ። ከአሁን ወዲህ የሚጠበቀው ለዚህ ክፍል ጥሩ አመለካከት ያለቸው የተቃዋሚ ድርጅቶች ምን ያህል ከዚህ አባባል እራሳቸውን ያርቃሉ የሚለው ነው። አሊያ የተባለውን አባባል መደገፍም ይመስላል።

መቼስ እንደተለመደው ኢሕአፓ የትግሬ ስብስብ ነው ይበሉን እንጂ ይህን የጅምላ ቅጣት ፓልቶክ ላይ የነበሩት የኢሕአፓ ደጋፊዎች በጣም ነው ያጣጣሉት ፣ ያወገዙት። ግልፅ እንዲሆን የምፈልገው አንዱ የተደበቀው የኢሕአፓ ድላችን በማንኛውም አገሪቱ ውስጥ በተደረጉ የጂምላ ቅጣት ላይ አልተሳተፍንም ፣ አለመሳተፍም ብቻ አደለም ግልፅ አውጥተን አውግዘናል። ጠላቶቻችንን ይህንን በመጠቀም የመርዝ ፕሮፖጋንዳቸውን ሲረጩ እንደከረሙ ግልፅ ነው ። ኤርትራ ላይ እርጉዝ አትግደሉ ስላልን የኤርትራ ቡችላ ተብለናል ። ብዙም ተፅፎብናል ። የሚያዋጣው የጅምላው ቅጣት ነው ተብሎም ለኢትዮጲያ ህዝብ ሌላ አማርጭ የለውም ተብሎ ተነግሮት ነበር። እውነቱ ግን ዛሬ ስንመለከተው ኤርትራም ከመገንጠል አልዳነችም ። ይህ እየታወቀ ዛሬም አልፎ አልፎ አንዳንድ ሆዳሞች የደርግ ጭፍጨፋ ያስከተለውን ውጤት በመካድ ኤርትራን ኢሕአፓን እንዳስገነጠለ ሲያወሩ እንሰማለን።እነዚህ የደርግ ካድሬዎች ተመልሰው ዛሬ በልዩ ልዩ የዘር ድርጅት ወሰጥ ተሰግስገው ኤርትራ ላይ ቢሮ ከፍተው ድሮ ከሚያወግዙዋቸው ጋር አብረው ይገኛሉ።አሁንም በተቀነባበረ ሁኔታ ኢሕአፓን ሲዋጉት እናያለን ።ለዚህም ነው ባለፈው ጽሁፌ „ ለማንም ተሸጠሽ ስልጣን ላይ ተመለሽ “ ያልኩት ።

ሌላው በሰሞኑ „የንፁህ ኢትየጲያዊ“ ማህረግ ያጣው ዶክተር ነገደ ነው ። የዶክተር ነገደ የህይወት ታሪኩ ከዚህ በፊት ተነግሮ ከሚያውቀው በላይ በደደቦች ሸንጎ ሲሰለቅ ነው የከረመው ። ዶክትር ነገደ ለዚህ ሽልማት ያልበቃው በጣም ለትንሽ ነው ። በውጭ ያለው ቅንጅት ተከፋፍሎአል ብሎ ተናግሮ ነው ። ይህንን መከፋፈል ከየት እንዳመጣው ለደደቦቹ ሸንጎ ግልፅ አልሆነላቸውም። አጋፋሪዎቹ እንደሚሉት ያልተደረገ ነገር ከየት አምጥቶ ነው የሚወራው ነው።አንዳንዴ እኔም ሳስበው በአንድ አለም

የምንኖር አይመስለኝም ። እኛ የሰማነውን እነርሱ አይሰሙትም ።ቅንጅት መንፈስ ነው የሚባለውን የግንቦት መንፈስ መባል አለበት ብሎ ቀይሮታል።የግንቦቱ ድል የቅንጂት ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ድል ነው ብሎ ሰፋ አርጎ ማየቱ በጣም ነው ያናደዳቸው። እነርሱ ይህንን እውንታ መቀበል ስላልፈለጉ የሚያዋጣቸው ዶክትር ነገደን መስደብ ነው ።

የደደቦቹን ሽንጎ ትተን ወደ ሌላው ስንሄድ ሌሊቱን ገትሮን ያሳደረን አዲሱ የአሲንባ የፓልቶክ ክፍል ፕሮግራም ነው ። ከታሪክ ማህደር ይባላል ።በዚሁ ድንቅ ለሆኑት ለአሲንባ አጋፋሪዎች ምስጋዬን አቀርባለሁ። ያቀረቡትም ማዘርን ነው።ማዘር የሰባ አምስት አመት አዛውንት ሲሆኑ አሁንም በትግሉ ውስጥ ያሉ ናቸው። ሁሉም እንቺ ሰለሚሉ እኔም አንቺ እላለሁ ። ለኢሕአፓ አባላት ፍቅራቸውን ለእርሷ መግለጫ ነው። ለመጀመሪያ ግዜ ማዘርን ያየኋሁት አንድ በአውሮፓ በተደረገ ስብሰባ የመጨረሻ ቀን ስብሰባውን በንግግር ለመዝጋት በተገኘችበት ወቅት ነው።በወቅቱ ብዙን ተሳታፊ በስሙ እየጠራች ስትስም ሴትየዋ የአባሉን ስም ዝርዝር በቃላቸው ነው የሚያውቁት ብዬ ገርሞኝ ነበር ።

አሁንም እንደበፊቱ ጥርት ባለው ንግግሯ አንድ በጣም ጠቃም ማሳሰቢያ ሰጥታናለች።የወደቁ ጓዶቻችንን ሱሪና ቀሚስ አሳይታ ደማቸው እንዲገለማን ጠይቃናለች ። ትግላችንን በሰፊው እንድንቀጥልም አሳስባናለች ።

ንግግሯን ስትጀምር ኢሕአፓ ገዳይ አደለም ገዳይ ደርግ ነው በማለት ነበር ። ከዳሮ ነጋሽ እስከ አየር መንገድ ስራተኞችና የሰራተኛ ማህበራት መሪዎች ተገድለው ለአስከሬናቸው ለጥይት የከፈልነው መሰሪያ ይዘው ተገኘው አደለም ። የተገደሉት የመብት ጥያቄ ስላቀረቡ ነው ብላ ስም እየጠቀሰች ጊዜንና ቦታን አንተርሳ ገልፃልንናለች ።

በኢሕአፓነታችው ልትኮሩበት ይገባል ብላ የበልጅግ አሊ አሮጊትና የሰፈሩ ሰው የሚያወራውን ዳግም አረጋገጣልናች ። ዛሬ የታሰሩ የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ ስንል እነደብተራውንም ጭምር መሆኑን እንደሚገባው አሳስባናለች ። አለበለዚያ ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ በተለይም ደግሞ ትንሾቹ ይፈቱ ሊሆን እንደማይገባውና የተረሱትም ወይም ደብዛቸው የጠፋውንም ሊያጠቃልል እንደሚገባው ግልጽ አድርጋለች።ሌሊቱን በሞላ ታዳሚዎቹ የሞቱትን ስም ዝርዝር በመፃፍ ሲያስታውሱዋቸውም ነበር ። በተደጋጋሚም ታሪኩ ሊፃፍ እንደሚገባው ከቤቱ ይሰነዘር ነበር።

ኢሕአፓነታችን ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ የሚለውን ጥያቄ እንድናነሳ ያስገድደናል። ይህንን ስንል መታሰራቸው በወያኔ የተረጋገጠላቸው ብቻ ሳይሆን በየተደበቀው የወያኔ እስርቤት ውስጥ ያሉትንም ማለታችን ነው ፡፡ ለመታሰራቸው ማረጋገጫ ከማንም አንጠይቅም ። መረጃውም ስለሌለን ጥያቄችንን አናቀርብም አንልም። ጥያቄያችን ከጠላቶቻችን ተቃውሞ ቢያስነሳም የምንፈራው ነገር የለም ። በጠላቶቻችን ቁጥጥር ስር ስላልሆን ጥያቄዎቻችንን ጠላቶቻችን አይወስኑልንም ። ስለዚህም ፦

ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ !!!!!!!!!
በሚል የዛሬውን ሰሞኑን በፓልቶክ አጠቃልላለሁ ።
ስለሁሉም እስረኞች የሚያስብ በሰላም ይክረም ፡፡
በልጀግ አሊ